## ስቴት ሴኔተር ማይክ ሲመንስ- ወረዳ 7

ለወረዳ 7 በትጋት እሰራለሁ

የ2021 ማጠቃለያ ሪፖርት

**ሊንከን ስኩየርን፤ አፕታውንን፤ ኤጅ ዋተርን፤ አንደርሰን ቪልን፤ ቦውማን ቪልን፤ ሬቨንስውድን፤ ሮጀርስ ፓርክን፤ ዌስት ሪጅንና፤ ኤቫንስትንን፤ ለማገልገል ዝግጁ መሆኔን ስገልጽ ከፍ ያለ ደስታና ኩራት ይሰማኛል።**

**ውድ ወገኖቼ፤**

እንደስቴት ሴነተርነቴና እንደ የወረዳችን ነዋሪነቴ ባገኘሁት ልምድ መሰረት የተዛባና ሁሉን በዕኩልነት የማያስተናግደውን ስርዐት ለመለወጥ ከመቸውም ጊዜ በላይ በበለጠ ዝግጁ ነኝ። እኔና ጽህፈት ቤታችን ረዘም ላለ ጊዜ ለኣካባቢያችን ነዋሪ፤ ለአነስተኛ የንግድ ባለቤቶችና ትምህርት ቤቶቻችን አስፈላጊውን ተጨማሪ ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፡፤

ከዚህ በመቀጠል እኔ የታገልኩላቸውና በአሸናፊነት ጸድቀው ሕግ የሆኑትን ላካፍላችሁ እወዳለሁ። አዎን ካለፉት ሁለት አስቸጋሪ አመታት ወዲህ ብዙ ሊሰሩና የነዋሪውን ችግር በመቅረፍ ወደ ተሻለ ኑሮ ለመሸጋገር የሚያስችሉትን ተግዳሮቶች ለማሳካት የበለጠ ትጋትና ስራዎች እንደሚጠበቅብን ይገባኛል።
ይህንንም በመረዳት እስከመጨረሻው ለመስራትና ያለመታከት ለመታገል በቁርጠኝነትና በጽናት መቆሜን አረጋግጥላችኋለሁ።

ለጥያቀአችሁ በሙሉ፤ ጽሕፈት ቤታችን ሁሌም ክፍት ነው።

አድራሻችን፦ 5533

ስልክ ቁጥራችን 773 769-1717

የእያንዳንዱን ፍላጎት ላማሳካት ትኩረት ሰጥተን እናንተን ለማገልገል ሁሌም ዝግጁ ነኝ።

እባክዎ በዚህ የክረምት ወቅት፤ የአይምሮም ሆነ የአካል ጉዳት እንዳይገጥምዎ እራስዎን ይጠብቁ።

የናንተው ማይክ ሲመንስ

የወረዳ 7 ስቴት ሴኔተር

የወረዳ ጽሕፈት ቤታችን

5533 N Broadway

Chicago, IL 60640

(773) 769-1717

**የስፕሪንግ ፊልድ ጽሕፈት ቤታችን**

M115 Capital Building

Springfield, IL 62706

(217) 782- 8492

**ስለእናንተ መብትና ጥቅም መታገል ተቀዳሚ አላማዬ ነው።**

- በዘመነ ኮሮና ከ400 በላይ ነዋሪዎቻችን የሥራ አጥነት ክፍያ እንዲያገኙ ረድቻለሁ።
- ተከራዮችን ኪራይ ለመክፈል የሚያስችል እርዳታ እንዲያገኙ ደብዳቤ አርቅቄ በ 28 ሴኔት ባልደረባዎቼን በማስተባበር እንዲፈርሙ አድርጌ ለአገረ ገዢው ቀርቦ እንዲጸድቅ በማድረግ አከራዮችምንም ታድጌአለሁ።
- ከ80000 ነዋሪዎች ጋር ኪራይ የመክፈል ዕርዳታ ለማግኘት እንዲያመለክቱ በቴክስት መለእክት ተለዋውጫለሁ።
- በ2022 ለሕግ አርቃቂው የስቴት ሴኔት አካል የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ለመቅረጽ የሚረዱ 8 ስብሰባዎችን ከባል አልባ እናቶች፤ ከአዛውንቶችና የአካባቢያችን ረጅም ጊዜ ነዋሪዎች ጋር አድርጌአለሁ።
- ከአፍጋኒስታን ለሚመጡ ስደተኞች የአንኙዋን ደህና መጥችሁ ስጦታ ዝግጅት ላይ ተሳትፌአለሁ።
- የLGBTQ+ ሕብረተሰባችን ላይ ያተኮረ ስለደረት/የጡት ነቀርሳ ኢግዚቢት አካሂደናል፡፤

**ከዚህ በታች ያቀረብኩአቸው ስድስቱም ሰነዶች ጸድቀው ሕግ ለመሆን በቅተዋል።**

HB 648: ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑት ተመጣጣኝ የሆነ ቤት ማስገኘት የሚያስችል

HB 3265፡ በግዳጅ ለሚደፈሩ ማገገሚያ ማዕከል በመሆን እንዲያገለግሉ ተጨማሪ ድርጅቶችን የሚፈቅድ

HB 3262: በሰው ልጅ ላይ በጾታ፤ በቀለም፤ በዘር፤ በሃይማኖትና፤ አካልጉዳተኝነት ላይ ብቻ ተመስርቶ ፖሊስ መጥራት በሕግ የተከለከለ የሙብት ጥሰት ስለሆነ በዘረኝነት ጥላቻ ወንጀል የሚያስከሰስና በገንዘብም የሚያስቀጣ እንዲሆን፡

SB 539: የሹመት ሂደትን ለማጠናቀቅ፤ ለተመረጡት የስራ መደቦች ግልጽነት፡ የሕዝብ ተሳትፎና ለክፍት የስራ ቦታው የተቀራረቡ የድምጽ ሰጪዎች ማስታወቂያ መውጣት ይኖርበታል።

SB 817፡ የሰው ልጅን በጸጉር አቀራረጡና ፋሽኑ ማለትም ሹሩባ፤ ጉንጉንና፤ የመሳሰሉትን ላይ በመመርኮዝ በትምሕርት ቤት አካባቢ የሚደረግን አድልዎ አጥብቆ ይከለክላል። በተለይም ወጣት ጥቁሮች ስልታዊ በሆነ መንገድ በትምሕርት ቤት ለዘመናት በጸጉራቸው ታላቅ መድልዎን ተሸክመው ኖረዋል. ይህን ያረጀና ያፈጀ ታሪክን የመለወጫው ጊዜ አሁን ነው።

SB 2133: ተላላፊ በሽታ በLGBTQ+ ሕብረተሰብ ውስጥ ያመጣውን ተጽዕኖ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳትና ለመለካት ያስችል ዘንድ፤ በስቴት ኤጀንሲና ሆስፒታሎች የሚሰበሰቡ የስነሕዝብ አወቃቀር ውሂብ ጾታንና የጾታ ዝንባሌን እንዲጨምር።

**ቀጣዩ ፍልሚያችን ከዚህ የሚከተሉት ላይ ያተኮረ ይሆናሉ**

**በተስብን ለመደገፍ፤-**

**SB 2132**: ወላጆች በተላላፊው በሽታ ምክንያት ኑሮአቸው ስለተጎዳ፤ በኢሊኖይ ስቴት ደረጃ በልጅ $600 የቀረጥ ምህረት እንዲደረግላቸው በትጋት እሰራለሁ።

**ሜዲኬድን ለማስፋፋት፦**

**SB 966**: አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል እንዲያካትትና አስፈላጊውን የጤና ህክምና በቀላሉ እንዲያገኙ ለማድረግ ገቢያቸው እስከ 200% በፌዴራል የድህነት ወለል ላይ ያሉንትንም እንዲጨምር አስፈላጊውን ትግል አደርጋለሁ።

**SB 828**: በኢሊኖይ ስቴት ውስጥ የአስረኞችን የመምረጥ መብት ለማስመለስ በትጋት እሰራለሁ። በገፍ የማሰርን ጉዳት ለመቀነስና ያደረሰውን የልብ ስብራት ለመጠገን ይህ የህግ ለውጥ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ።

**ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የመገናኛ መንገዶች በሙሉ ልታገኙን ትችላላችሁ።**

Instagram; @SenMikeSimmons
http;//senatormikesimmons.com/
facebook:@SenMikeSimmons
Twitter: @SenMikeSimmons

ጠቃሚ ቁጥሮች/ Important numbers
CARE FOR REAL
(773) 769-6182

REFUGEE ONE
(773) 989-5647

DOMESTIC VIOLENCE
SUPPORT NUMBER
Apna-Ghar: (773) 883-4663
24-hours Helpline (773)334-4663

LGBTQ+ SUPPORTIVE

SERVICE TREVOR PROJECT

SUPPORT NUMBER

(TREVOR LIFELINE)

(868) 488-7386

ILLINOIS DEPARTMENT OF HUMAN SERVICES

(MEDICAID, SNAP)

211

ATTORNEY GENERAL'S

FRAUD HOTLINE

(800)386-5438

CALL4CALM TEXT LINE

EMOTIONAL SUPPORT

Text Talk to 552020 for English

HABLAR for Spanish

CDPH COVID-19 HOTLINE

(312)747-9884

ILLINOIS DEPARTMENT OF EMPLOYMENT SECURITY

(800)244-5631

ILLINOIS DEPARTMENT ON AGING SENIOR HELPLINE

(800) 252-8966

MEALS ON WHEELS

(773)661-4550

SENIORS: (312) 744-4016, PRESS 4

INDIVIDUALS WITH DISABILTIES

(312) 744-6673

NATIONAL SUICIDE PREVENTION HOTLINE

(800) 273-TALK (8255)

NORTHEAST (LEVY) SENIOR REGIONAL CENTER

(312) 744-0784

NORTH AREA COMMUNITY SERVICE CENTER

(312) 744-2580